# ***<u>በዘመን ወያኔ</u>***

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*ምን ተወደደ ?*
*ኑሮ፤*
*ምን ረከሰ ?*
*ሮሮ፤*
*ምን ይበላል ?*
*ጓያ፤*
*ምን ይጨሳል ?*
*ጋያ፤*
*ምን ተረሳ ?*
*ጀግንነት፤*
*ምን ተለመደ ?*
*ፍርሃት ::*

*ምን ይሠራል ?*
*ጥፋት፤*
*ምን ይሰማል ?*
*ውሸት፤*
*ምን ይዘንባል ?*
*ዕንባ፤*
*ምን ይበቅላል ?*
*ገለባ ::*

*ማን ታሰረች ?*
*ሃቅ፤*
*ምን ወለደች ?*
*ጭንቅ፤*
*ምን ይፈሳል ?*
*ደም፤*
*ምን ይዳኛል ?*
*ቂም ::*

*ምን ይዘራል ?*
*ጥላቻ፤*
*ምን ይበቅላል ?*
*ፍራቻ፤*
*ምን ይጻፋል ?*
*ውሸት፤*
*ምን ይሰማል ?*
*ቅሌት፤*

ምን ይታወጃል ?
ጦርነት፤
ምን ይታጨዳል ?
ሞት፤
ማን ሞተ ?
ዕድገት፤
ምን ተለመደ ?
ስርቆት፤
ማን ነገሠ ?
ክህደት ።

ምን ተሸጠ ?
አገርና መሬት፤
ማን ተ'ኳሰሰች ?
ነፃነት፤
ማን ተሞካሸ ?
ባንዳነት፤
በዘመነ ወያኔ፤
ወይ አገሬ ! ወይ ወገኔ !
ወይ እኔ ! ወይ እኔ !

አንድ ቀን
ለአገሬ ኢትዮጵያና ለወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ።